# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የስብከት ዘመን ሁለተኛ ሰንበት

ከታህሣሥ ፯ ቀን ጀምሮ እስከ ታህሣሥ ፳፰ ቀን ያለው ዘመን ዘመነ ስብከት ይባላል። ምክንያቱም ነቢያት የጌታን በሥጋ መምጣት አምልው አስፍተው በትንቢት በትምህርት በማስተማር መስበካቸውን ቤተ ክርስቲያን እያሰበች ሰውን ለማዳን ወደ ምድር የመጣውን አምላክ የምትሰብክበት ወቅት በመሆኑ ነው።

### የዕለቱ ምስባክ

ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ
እማንቱ ይምርሐኒ ወይሰዳኒ ደብረ መቅደስከ
ወውስተ አብያተከ እግዚኦ

ብርሃንህንና እውነትህን ላክ
እነሱ ይምሩኝ
ወደ ቅድስናህ ተራራና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ

*መዝ ፵፪፥፫-፬*

ምስጢር (ትርጉም)፥ ብርሃን ጽድቅ እውነት ልጅህን (ወልድን) ላከልኝ እርሱ መርቶ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያገባኝ ዘንድ ማለት ነው።

ወንጌል፥ ዮሐ ፩፥፩-፲፱
ቅዳሴ፥ የአትናቴዎስ ቅዳሴ

የዘመነ ስብከት ሁለተኛው ሰንበት ብርሃን ይባላል። ነቢያት የነፍሳችን ብርሃን ይወለዳል ብለው ስለመስበካቸው፤ እውነተኛ ብርሃን ይመጣል ብለው ስለመስበካቸው የሚታሰብበት ቀን ሲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊ ብርሃን መሆኑ ይሰበካል ይመሰገናል።

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፲፫፥፲፩ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፩፥፩ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፮፥፲፪-፲፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### *የዕለቱ ትምህርት*

## እውነተኛ ብርሃን

ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ሕይወት የሆነች ብርሃን የገለጠ፤ ጨለማ ያላሸነፈው፤ በጨለማ ውስጥ የሚያበራ «ብርሃን ዘበአማን - አማናዊ ብርሃን» የተባለ፤ አንቀጸ ብርሃን ከተባለች ድንግል የተወለደ፤ ሕይወትን የወለደ የብርሃን አባት አምላከ ብርሃን፤ ወላዴ ሕይወት ከተባለ ከእግዚአብሔር አብ ወላዴ ብርሃን የተወለደ፤ የማይመረመር «ብርሃን ዘኢይትነገር» የማይነገር ብርሃን የተባለ፤ «ዘእንተ ውስጥ ዓይነ አብራህከ ወጽልመተ ኅሊናከ» የኅሊናችንን ጽልመት ያበራ፤ ዓይነ ልቡናችንን የገለጠው ብርሃነ ፍጹማን፤ ወልደ አምላክ ሕያው - የሕያው አምላክ ልጁ የፍጹማን ብርሃን ነው።

ስለዚህ ብርሃን ሊመሰክር ዮሐንስ ተላከ ሲመሰክርም ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም መጣ ብሎ መሰከረ። ይህም ብርሃን በልቡናችን ውስጥ የሚያበራው ነው (፪ኛ ጴጥ ፩፥፲፱)። የዓለም ብርሃን ነው (ዮሐ ፰፥፲፪-፶፱) ለአሕዛብም ብርሃን እንደሆነ ቀድሞ ተወስኖ ነበር (ኢሳ ፵፱፥፮)። ይህ ብርሃን ከመሰናከል ያድናል እንቅፋት ከመመታትም ሆነ መሰናክል ያድናል እንቅፋቱንም ያሳያል።

አንባቢ ሆይ፥- ይህ ታላቅ ብርሃን በርቶልሃልን? በብርሃኑ ተመላለስ። ሥራህ ሁሉ በብርሃኑ ይገለጥ፤ ዕውርም ሕይወት ካለህ እርሱ ብርሃነ ዕውራን - የዕውራን ብርሃን ስለሆነ ማየትን ይሰጥሃልና አትራቀው። ሥራቸው ክፉ የሆኑ ሰዎች ብርሃንን እንደሚጠሉ አንተም ከብርሃኑ አትሸሽ፤ በብርሃን የሚደበቅ ሥራም በብርሃንም የሚያሳፍርህ ሕይወት ካለህ በንስሃ አስወግድ በጨለማ አትኑር። «ዐይነ ዘማዊ ይጸንህ ጽልመተ - የዘማዊ ዓይን ጨለማን ይጠብቃል» እንደተባለ በጨለማ የምትኖር ከሆነ ጠላትህ ሳታየው ያጠፋሃል።

ስለዚህ በብርሃኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አምነህ ብርሃን ለብሰህ ብርሃን ተጎናጽፈህ ከውሉደ ብርሃን ጻድቃን ጋር በየማነ አብ ለመቆም ትጋ።

<u>ጥቅስ ከመዝሙረ ያሬድ</u>

1. «ብርሃን ዘመጽአ ውስተ ዓለም ዚያበርህ ላዕለ ጻድቃን ምርዓዊሃ ለቤተ ክርስቲያን ይርዳዕ ዘተኃጉለ ያስተጋብእ ዝርዋነ መጽአ ኀቤነ»
   በጻድቃን ላይ የሚያበራ ወደ ዓለም የመጣ ብርሃን የቤተ ክርስቲያን ሙሽራ የጠፋውን ሊፈልግ የተበተነውን ይሰበስብ ዘንድ ወደ እኛ መጣ። (መዝሙር)

2. «በከመ ይቤ ጳውሎስ ንግድፍ እምላዕሌነ ኩሎ ምግባረ ጽልመት ወንልበስ ወልታ ጽድቅ እስመ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽአ ውስተ ዓለም ንዑ ናንሶሱ በብርሃኑ»
   ጳውሎስ እንደተናገረ የጨለማውን ሥራ ሁሉ እንጣል፤ የጽድቅን ወልታ እንልበስ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም መጥቶአልና በብርሃኑ እንመላለስ (እዝል)

3. «ብርሃን ዘበአማን ዘያበርህ ለኩሉ ሰቡእ ለእለ ይነብሩ ውስተ ዓለም»
   አማናዊ ብርሃን (ጠፈር ደፈር የማይከለክለው የሌሊት ጨለማ የማያሸንፈው) በዓለም ላሉት ሁሉ የሚያበራ። (ቅዱስ ኤፍሬም - ውዳሴ ማርያም)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።